# አወይ ቤተክሲያናችን !!!

ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ
ሚያዝያ ፩ ቀን ፪ሺህ ፫

## ቤተክሲያን - የችግር-የጭንቅ አስወጋጅ አሊያም አቃለይ ነበረች

### በእኛ ዘመን ራሷ ችግር ኾነች!

ለችግርነቷ ምንጭ የኾኑት ደግሞ ተከብረው በበለጠ የሚያስከብሯት ተወድደው በበለጠ የሚስወድዷት ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቷ እስከ ዲያቆናቷ ድረስ በተዋረድ ወድደው የተቀበሉትን የአጋልጋይነት ኃላፊነትና ግዳጅ በሥርዐቷ መሠረት ሲፈጽሙላት ነበር። ክህነት ማለት ማገልገል፡- ብሎም ካህን ማለትአገልጋይ ማለት ነው ብላችሁ አስተምራችሁን የለ? ማንኛችን እንኾን የረሳነው? አስተማሪዎቹ ወይስ እኛ ተማሪዎቻችሁ?

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሊኖራት ሲገባ በረከቱባት። በዘውድ ሥርዐት ባለ ዘውዱ “የቤተ ክርስቲያኗም የበላይ ጠባቂ !” ስለነበረ እንዲህ ዓይነቱ ኪሳራ አይሞከርም ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ የቤተክርስቲያኗ የበላይ ጠባቂ ነበርና! (የዘመኑ ዐዋቂዎችና ተራማጆች “ ሃይማኖትና መንግሥት መለየት አለባቸው!” ብለው ከመራቀቃቸው በፊት የኢትዮጵያችንን አንድነትና ነጻነት( አኹን ኹሉም የሚደገግበትን አኩሪ ነጻንትና መንፈስ የተጎናጸፈው በዘውድና መስቀል በኅብረት ጠባቂነታቸው ያቆዩለት እንደኾነ ማስታወሱ ከስህተት ያድናል። ከነቀፋ በፊትም ትንሽ ስለ ባለዘውድ አገሮች በ’መግልጎል’ እንኳን መመራመሩ ይጠቅማል። (ጉጉል)

የዚህች ጽሑፍ ትኩረት በይበልጥ ውጪ ባለው ሲኖዶስ ላይ ሲኾን አገር ውስጥ ላለውም “መልዕክት” ይኖረዋል። ቃሉን የመረጥሁት አስቤ ነው። ከዚህ በፊት ኹለቱንም ለምኜ፡- ተማጥኜ፡- ተለማምጬ ለአገሬና ለቤተክርስቲያኔ ምንም አላገኘሁም።

ዕርቅ ፈረሰ ውግዘቱ ቀለጠ! አይ አለመታደል። የውጪው ሲኖዶስ ቃል-አቀባይ/የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ በኢሳት ላይ የመጀመሪያው መግለጫቸው ‘ ብዙ ሥራ አለብን …ገንዘብ ያስፈልገናል…ብዙ ቆመሶች እንሾማለን!’ ከመልክቶቻቸው ዋናዎቹ ነብሩ።ብዙዎቻችን ይህን ስንሰማ ቆዝመን(አዝነን፡- ተክዘን) ሳለን የቤተክርስቲያኖች አደን መጧጧኡፉን ሰማን። ይህም

ቤተክርስቲያናቸውን ገዝተው/አሠርተው በሰላም ‘ አቤት! አቤት! ተመስገን’ የሚሉትን ወንድማማቾችን/እህትማማምቾችን ለየ፤፤ አጣላ! አራራቀ።ከፋፈለ። በዐቢይ የተከፋፈላችሁት ሲያሳዝነን፤- አገር ያሉት በገዥዎቹ ጫና ጭምር ዉጪ ባለነው ላይ የሚያደርጉትን ግፍና ተንኮል እናንተም የውጪዎቹ ትፈጽሙብን? ጠብና ክፍፍል ባገራችን ላይ ሞልተው ተርፈው እያሉ በውጪዎቹ ረዳትነት የስደት መጠነኛ የመንፈስ ርጋታችንን ታሳጡን? ጭፍራ ለማበርከት! ለምኑ? የውግዘት ተካፋዮችን በማብዛት ከውግዘት የነጻ የቤተክርስቲያኗ ልጅ እንዳይኖር መጣጣር?

## በውጪው ሲኖዶስ ስር ለማሰኘት!

መቼ ይሂ ብቻ?! በሲኖዶሶች ተብዬዎች መካከል በገላጋይነት የሚገባ ለማሳጣት? ይህማ የነስብሀት ነጋ አስፈጻሚ መኾን አይደለም? በመጀመሪያው ጽሑፌ በጥር ፫ “ቤተክርስቲያናችንን እናድን…መስጊዳችንንም” ላይ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቤተክርስቲያናችንንም ማዳከም እንደሚያስፈልግ የተለሙ መኾናቸውን ብታውቁትም አስታውሼያችሁ ነበር። የምን ተባባሪነት ነው? ከውስጥም ከስድስት ያላነሱ የተለያዩ ስሞችን ይዘው በ’ተሃድሶ’ አላማዎች መራወጣቸውንና የከፋ ከመኾኑ በፊት የሃይማኖታችንን ልሂቃን መርጦ ማነጋገሩ ከባሰ መለያየት ስለሚያድን እንድታስቡበት ለምኜ አልነበረም? ታዲያ በውጪ ያለነውን በመከፋፈል ድክመታንን ማብዛት ጥቅሙ ለማን ነው? ለቤተክርስቲያናችን መኾን አለመኾኑን ለማወቅ ጠንቋይ እንፈልግ? የምፍትሄ ምርጫችንን አጣበባችሁት እኮ! እንዲያውም ፈጽማችሁ ልታመክኑት ነው።

ስለዚህ ውጪ ያለነውን በገለልተኝነት እንድንቀጥል አታጣሉን። አትከፋፍሉን። ውግዘት ውስጥ አታስገቡን። ነገ ለማስታረቅ፤- ፈቃዱ ይኹንና!፤ የውጪ ሽማግሌዎች ከመፈለግ እንዳን። ተዉን!!!

ውስጥ ላሉት ልክ ውጪ እንዳሉት ‘ በተሃድሶ’ ስም የተሰለፉትን የሚያነጋግሩ ዕውነተኛ የሃይማኖታችንን ምሑራን መርጣችሁ በጥሞና እንዲያነጋግሩ ማድረጉ አይጠቅምም?

እንዲያውም እኮ ለዚህ ዐቢይ ጉዳይ የኹለቱም ሲኖዶሶች ተመራጮች በአንድ ኾነው ስልታቸውን አዋድደው በመከራከሪያዎቻቸውም ተስማምተው ቢገጥሙ ለዚች ምስኪን የልጅ አልባ ለኾነችው ቤተክርስቲያን የተስፋ ጭላንጭል ታተርፉላታላችሁ።

እስቲ ትንሽ ሰፋ ላድርገው፡- በገለልተኛነትም ያሉት ምሑራን ተመራርጠው አስፈላጊዎቹን ዝግጅቶች አጠናቅቀው ቢችሉ ኹሉም በአንድነት ካልኾነ

ስልታቸውንና ሙግታቸውን ለኹለቱም ለትችት አቅርበው (ሽማግሌ ሊ.ጳጳሳት ስላሉባቸው) ከወንድሞቻችን ጋር በፍጹም መንፈሳዊነት ዕውነትን መነሻና መድረሻ አድርጎ በመነጋገር መፍትሄ መፈለጉ ይጠቅም ይመስለኛል፤ ባገር ውስጥ ካሉት ጭንቆች፦

" አንዳንዶች የካህናትና የዲያቆናት ችግር አላላውስ ሲላቸው ሌሎች ደግሞ ጧፍ ፣ እጣን ፣ ዘቢብ እና መሰል መገልገያዎች እጦት ይስተዋልባቸዋል፡፡ "

ላፍቶ ሌንቃ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በሀዲያ እና ስልጢ ሀገረ ስብከት ውስጥ…እና ለመናገር የሚያስችል በቂ መረጃ የሌለ ቢሆንም ዘመናትን እንዳስቆጠረ የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ ቦታው በአካባቢው ላይ ያሉ የጥንት አባቶች ሲጠቀሙበት የነበሩ ዋሻዎች ፣ በውስጣቸው የተገኘው የመስቀል ምልክት እና ፅሁፍ ለዕድሜ ጠገብነቱ ምስክሮች ናቸው፡፡ የላፍቶ ሌንቃ መድኃኔዓለም አካባቢ ምዕመናን ልጅ ወልደው ክርስትና የሚያስነሱበት ፣ በስርዓተ ቤተክርስቲያን የሚያሳድጉበት ፣ ቅዳሴ የሚያስቀድሱበት ፣ ለራሳቸውም ይሁን ለልጆቻቸው ስጋወ ደሙ የሚቀበሉበት ፣ የወንጌል አግልግሎት የሚያገኙበት ፣ በአላትን የሚያከብሩበትና መሰል አገልግሎት የሚያገኙበት ቤተ ክርስቲያን የላቸውም …እስከ አሁንም ድረስ በላፍቶ ሌንቃ የሥላሴ ልጅነት ጥምቀት ያልተጠመቁ ህፃናት እና ወጣቶች ያሉ ሲሆን አንገታቸው ላይ ማህተብ በማሰር **‹‹እኔ ክርስቲያን ነኝ››** በማለት በአህዛብ መካከል እየመሰከሩ ይኖራሉ፡፡ ላፍቶ ሌንቃ መድኃኔዓለም እንደ ቤተክርስቲያን የሚያገለግለው ዋርካ/ዛፍ/ ሲሆን ከስሩ ስዕለ መድኃኔዓለምን በማስቀመጥ ይጠቀሙበታል፡፡ በፊት የነበረው ቤተክርስቲያን በተለያየ ጊዜ የተነሱ አፅራረ ቤተክርስቲያን ለሦስት ጊዜ ያፈረሱት ሲሆን ለመጨረሻ ጊዜ በ1971 ዓ.ም በአህዛብ ተቃጥሏል፡፡

በአካባቢው ያሉት 70 የማይሞሉ ክርስቲያኖች ሃይማኖታችንን አንክድም ማተባችንን አንበጥስም በማለት ያለ መምህር በመፅናት ለአስርት ዓመታት ቆይተዋል፡፡ እነዚህ ምዕመናን በአንዲት እምነታቸው ምክንያት ባለፉት 33 ዓመታት ያሳለፉትን መከራ ተናግሮ መጨረስ የማይቻል መሆኑን በቦታው በህይወት ያሉ የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ የቤተክርስቲያኑን ይዞታ አንሰጥም በማለታቸው ምክንያት ለበርካታ ጊዜያት ታስረዋል ፤ ተገርፈዋል ፤ ብዙም መከራም ደርሶባቸዋል፡፡ "

*

ምናልባት ከእኔ የበለጠ የምታውቁትን አንድ ታሪክ ለማያውቁት ልንገር።

በጥንት ዘመን ለሩሲያ ኦርቶዶቅስ ቤተክርስቲያን አንድ ሊቀ-ሊቀ ጳጳሳት ኾነው ሲመረጡ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን ኹሉ እየዞሩ ማየትን መረጡ። ዞረው ዞረው "አዳረስን ወይ?" ብለው ሲጠይቁ "አዎን ግን.." ይሉና መዋሸት የማያውቁት ጳጳስ ዝም ይላሉ። ፓቲራርኩም "ምነው 'ግን' ብለህ አቆምህ?" ቢሏቸው። "አይ አንዲት ትንሽ ደሴት ውስጥ ሦስት ሰዎች ብቻ መቅረታቸውንና.." ሲሉ ፓትሪአርኩ " እነሱስ ለምን ይቅሩ ወስዱኝ!" ብለው ይሄዳሉ።

ጀልባቸው ስትቃረብ ሦስቱ ሰዎች እየሮጡ ሄደው ይቀበሏቸዋል።

| | |
|---|---|
| ፓትሪአርኩ | " ክርስቲያኖች ናችሁ?" |
| ደሴተኞቹ በጥሞና | " አዎን፤፤' |
| ፓትሪአርኩ | "ትጸልያላችሁ?" |
| ደሴተኞቹ | "አዎን፡" |
| ፓትሪአርኩ | "ምን እያላችሁ ነው የምትጸልዩት?" |
| ደሴተኞቹ | " እናንተ ሦስት ናችሁ፦ እኛም ሦስት ነን ጠብቁን" እያልን |

ፓትሪአርኩ ጥሩ ነው ብለው አቡነ ዘበሰማያትን አስጠንተው የመልስ ጉዟቸውን ይጀምራሉ። ትንሽ እንደሄዱ፦
ቀዛፊው በመደነቅ " እነዚያ ሰዎች በውሀ ላይ ይሮጣሉ!" ይላል

ፓትሪአርኩ ለማረጋገጥ ዘወር ሲሉ ዕውነትም ሰዎቹ በውሀ ላይ ይሮጣሉ። ቀዛፊውን እንዲያቆም አዝዘው በመደነቅ ተነስተው "ምነው? ምነው" ቢሉ " አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር.. ብሎ ምን ነበር? " ሲሉ ይጠይቃሉ፤፤

ፓትሪአርኩ "ግድ የለም እናንተው ትጸልዩ እንደነበረው ቀጥሉ፤፤" እንዳሏቸው ሰምቻለሁ/አንብቤአለሁ
የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!!

## ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

## ***በላፎ ሌንቃ መድኃኔዓለም አካባቢ ያሉት ቅርሶች እንዳይዘርፉ አደራ!